ይስማዕከ ወርቁ

# የወንድ ምጥ



http://ethzare.wordpress.com

## ምስጋና

- ☛ለዓለሙ ቢያድጌ ጌታሁን
- ☛ለበዛብህ ስሜነህ
- ☛ለኮተቤው የጥበብ ወጌሻ የንታ የሻው ተሰማ
- ☛ለጋሼ ሥዩም ተፈራ
- ☛ለደራሲ ፍቅረ ማርቆስ ደስታ
- ☛ለገጣሚ ለበለው ገበየሁ



## መግለቢያ

ከሕይወት ምድጃዬ ጥደት........የእውነት፣ የሕይወት፣ የውበት፣ የመኖርና ያለመኖር ውህደት እንፋሎት ያሰገነፈለኝን እነሆ:: ከቅሰሜ ቅስም፣ ከላቤ ወዝ የነሱ የነፍሴን እብራክ ከፋዮች እነሆ::

እንበለ ዘርዓ ሰብዕ አልተፀነሱም፤ ከህያዋን የዘር ፍሬ በሰንኝ የፀነስኳቸው ናቸው:: በየቀኑ እየተወለደ በየቀኑ እየሞተ ሲድህ ከሚኖር እኔነቴ የተወለዱትን እነዚህን ልጆቼን እነሆ አቆንጇልኝ:: ከልጆቼ መሀል ንፍጥ እፍንጫው ስር የተለጎደበት ብታገኙ አደራ በምግባር መሀረማችሁ ጥረጉለት እንጂ ንፍጡ የህይወቱ አካል እንዳይደለ ቆጥራችሁ አትጥሉብኝ:: ወይም እንደማናቸውም ፍጡራን (ቆንጆውም አስቀያሚውም እንደሚኖር) እስከንፍጣቸው እንዲኖሩ ፍቀዱላቸው:: በር ላይ ቆሜ ብዙ ከማስቆማችሁ ግቡና ልጆቼን እዩአቸው፤ ከምድጃዬ ዳር «ዕርቃናቸውን» እሳቴንና እሳታችሁን እየሞቁ ታገኟቸዋላችሁ:: ግድግዳ አልባ ቤቴን ከፍቼ በጊዜ ግቡ ብያለሁ፤ ግቡልኝ::

ይስማዕከ ወርቁ ፲፱፻፺፱ዓ.ም



http://ethzare.wordpress.com

## መክስተ አርዕስት

**አርዕስት** **ገጽ**

ሕይወት በነጠላ.....9
የፈጣሪ አስከሬን.....10
ኑ ሞትን ቅመሱ.....11
ሳይነጋ.....12
ስንፈተ ሰብዕ.....13
ውርዝው ነጌ.....14
የማይከፈት በር.....15
ካውያ.....16
ፔንግዊን አፍሪካ.....17
ጫፍ አልባ ቁልቁለት.....19
ባዶ አርጊኝ.....20
ሰርዶ.....21
ከራስም ሲታነስ.....22
ድፍርስርሱ ደሜ.....23
ሰሞነኛ.....24
ሰይጣን የታደለው.....25
ተመየጢ ፈላሲት.....27
ዝረፍ ዝረፍ አለኝ.....29
ተላለፉ ሲለን.....30
አንጋፋው ሱሪዬ.....31
አብረን ብንተኛ.....32
መንገደ ምርቃና.....33
አመክንዮ.....34
ፈሶሎጂ.....35
ኪርያላይሶን.....38
ምነው አምና በሞትኩ.....39
እንዲሞቀው በድኔ.....40
ይቀረኛል.....41
ሲያጋጥም.....42



**ገፅ**

ልኬታ.....43
ሳይቀርቡ ቆርቦ.....44
ሰቆቃው ቂል.....45
ሀሳሲ ፈላሲ.....46
ዝግመተ ለውጥ.....47
የጥጃ ምስል.....48
መቅደሴን.....49
ይበለኝ.....50
ሕልም አልም.....51
አዕምራ ለሔዋን.....52
ዕንባ ማኪያቶ.....54
የግጥም ጅምናዚየም.....55
የአፈ ጉባኤው መዶሻ.....56
ኩርኩም.....57
የገሀነም መዝገብ.....58
ሉልነት? ሎሌነት?.....59
የትኋን ሽቶ.....60
አግቡኝ.....61
ጢም አልባ.....63
ብርሌ ሲነቃ.....64
ልናነጋ ተኛን.....65
አያቴ.....66
ጉባኤ ፍና.....67
ኤዲት ይደረግ.....68
ሚዛኑ.....69
ከ'ኔ በጥቂቱ.....70
አቤቱ.....71
ትበጥብህ?.....72
ዘመነ መንሱት.....73
ስሳት.....74
የወንድ ምጥ.....75



http://ethzare.wordpress.com

**ዛሬ ልደቴ ነው፤ ነገም ልደቴ ነው፤ ትናንትም ልደቴ ነበር።**



# ሕይወት በነጠላ

አፈር ጥጡን ለቅሞ፣ አባዝቶ....አሳስቶ
በእፍታ ብረቱ፣ አዳምጦ. . . አጥርቶ
በእስትንፋስ ደጋኑ፣ ነድፎ. . . . አሰፋፍቶ
ልቃቂት አልቶ፣ በህላዌ እንዝርቱ፣ ፈትሎ...አመልምሎ
ሕይወት ነጠላ ነው፤
አምላክ የሸመነው፣ አምላክ ቀጭን ፈትሎ።
ዘሀውና ማጉ፣ ነው ተመሳቃዩ፤ ኑሮ ጥልፍልፉ።
ሞት ጥለትም ጌጡ፤
ለኑባሬው ጣዕም ለብኩን ምዕራፉ።
መጋጠሚያ ውሉ፣ የመሀል ስፌቱ፣ ነጠላ ጥንደቱ፣
ልዩነት ውህደቱ፣ጥበብ አንድነቱ፣ አብሮነት ሐሴቱ፤
የሚንፈራገጠው አልቋጭም ባዩ  በዘርፍ ቋጭቱ፣
እምቢ ልኑር ባዩ፣
ነጠላ ቀጭኑ ህይወት ተፈታዩ፣
...... ላ' ንዱ ተዘቅዝቆ፣
...... ለሌላው ሽብርቆ፣
ላ' ንዳንዱ ማሰሻ፣  የመርገምት ጨርቁ
ላንዳንዱ ነጭ  ኩታ፣
ድግ ሆኖ 'ምናየው ...... ላ' ንዱ ደግሞ ማቁ፣
ሕይወት ነጠላ ነው፤
አምላክ ቀጭን ፈትሎ፣  አምላክ የሸመነው፤
ሞገሱና ዕድሜው ግን፣  እንደ ለባሹ  ነው ።



http://ethzare.wordpress.com

## ሳይነጋ

ይህን ወረቀት 'ማበላሸው
በብዕሬ አንባ 'ማቆሸሸው
ሳይነጋ የወለድኩት ልጄ
ክሴን እንዳይጥፍበት ነው።



## ስንፈተ ሰብዕ

የቱኛ በቀሉ ጎርፍ የደፈጠጠው'
ተኝቶ ያፈራል ትል እያሳመጠው።
ድንጋዩን ባይጫን አፈሩን ሳይለብሰው'
መፈርጠጡስ ይቅር፣ መዳህ ያቅተዋል ሰው!?



http://ethzare.wordpress.com

## ውርዝው ነኜ

የዝሆን አዳኞች፣ ዛፉን አከርክረው ይቀቡታል ጭቃ::
እንዱ አቢይ ነኜ
የዝሆን እሮኜ
ሲደገፍ እንዲወድቅ ከዛፉ እንዳይነቃ::
አበይት ነኜያት - - - ይሰበሰቡና
ሲያነሱት ሲያቅታቸው
በኩምቢያቸው ገፍተው
ጩኸት ያሰማሉ
ውርዝው ነኜ ይምጣ ያንሳልን እያሉ::
ውርዝው ነኜ መጥቶ - -
በጠንካራ ኩምቢው በኃይሉ ተገፍቶ
የወደቀው ዝሆን ይነሳል በርትቶ::
የታል የኛ ዝሆን የኛ ወጣት ነኜ
ተደግፈን ስንወድቅ ስንሆን እሮኜ
ገፍቶ የሚያስነሳን የኛ ውርዝውሳ?
እንደ መቅደላው ፈርጥ እንደ ቋራው ካሳ
ኢትዮጵያዊ ነኜ ምናለ ቢነሳ?



## የማይከፈት በር

ለግቶ - - - ፈክቶ - - -ስቆ
ለክሮ- - - መሽቶ - - ባርቆ
ተምዘግዝጉ - - - ወድቆ
ተንገዳግዶ - - - ደቆ
ዞሮ- - - ናላ አዙሮ
በውሉደ ጌሾ - - - በጥንስሶች ለክሮ
ቤቱ ካሳት ጎጆው - - - ከበር ተገትሮ
አይከፈትልህ ሲለው ለሰካራም
ግድግዳውን እንጂ በሩን እያንኳኳም::



http://ethzare.wordpress.com

# ካውያ

ካውያ ቢኖረው ለሰው እንደሱሪው እንደልብሱ
ሲጨማደድ ቀጭን ቆዳው ሲጨማተር ገበር ነፍሱ
ካውያ ቢኖረው ለሰው ካውያ ቢኖረው ለ'ሱ
የአያቶቹን ገፅ የአያቶቹን ገላ ቢተኩሰው በታደሱ::

ጰ ጰ ጰ





# ፔንግዊን አፍሪካ

ኦ እናት ፔንግዊን ኦ እናት አፍሪካ ፀሊም ወፀአዳ
የእኔነቴ ማጀት የእኔነቴ ጓዳ
ጀርባሽ ጥቁር ካባ ፊትሽ ነጭ ጋቢ
በማያበር ክንፍ ሁሌ ተርገብጋቢ
ለሆድሽ ደመኛ ለእኔ ተንገብጋቢ::
ሆድሽን እያማረው ጠመሽ ለእኔ አጥጋቢ::
ጠግቤአለሁና ከአፍሽ በተከካ
ከአፍሽ በተቦካ
አድጌአለሁና ከአፍሽ በተከካ



http://ethzare.wordpress.com

ከአፍሽ በተቦካ

ኦ ለናት ፔንግዊን ኦ እናት አፍሪካ
አንቺ የፍቅር እምባ አንቺ የእናት ዲካ
የመቀበል ንፉግ የመስጠት ቋርፍ ዋርካ
ከኢምንት ውቅያኖስ የኔ ቅድመ ሕዋስ የሕላዌ ባርካ
መብረር አስተምሪኝ ይህን ፍቅር ልስበክ ከአውሮጳ-አፍሪካ::
ኦ እናት ፔንግዊን ኦ እናት አፍሪካ
ዋካ - ዋርካ - - ዋካ
የነጭና ጥቁር የአንድነት ሰንደቅ
የእርግብ እና ቁራ ቅኔ ሰምና ወርቅ
ካባ እንደ ደረበ የእቋቋም መርጌታ ምሳሌሽ ከመሊቅ
የነጭና ጥቁር የእርቃችን ሰንደቅ
ሁኚ ሐሳዊው ነጩ ርግብ ይልቀቅ::
ኦ እናት ፔንግዊን እንደ ገዴ አሞራ ፀሊም ወፀአዳ
ከአፍሽ የተከካው ነው እንዴ የኔ እዳ?
ኦ እናት ፔንግዊን ከማሁ ለገዴ
ኦ እናት አፍሪካ አንቺ እናት ዓለም
ነፃ ስጦታ እንጂ ፍቅር ዕዳ አይደለም
የሚሰጥ እጅ እንጂ ፍቅር ኪስ የለውም::
ኦ እናት ፔንግዊን
ኦ እናት አፍሪካ ቅኔሁ ለዳርዊን
ዕዳ አይደለም እንጂ ፍቅርሽ ዕዳ ቢሆን
ትቼው ረስቼው የዕዳ መዝገቡን
ከፅንስ እስከ ልደት ሁልቆ መሳፍርቱን
የተበደርኩትን የተበደሩቱን
መች በቻልኩ እከፍልሽ ያኔ ለቋቋሽኝ የእንቁላል ቅርፊቱን!?
ኦ እናት ፔንግዊን ኦ እናት አፍሪካ
አንቺ እናት አለም ጥቁሯ አንታርቲካ
ኤሊዎች ቀደሙሽ ድክድክ ስትይ ላትይዥ ስታደቢ
እግሮችሽ አጠሩ
ክንፎችሽ ገረሩ
ጎንበስ ቀና ስትይ በሆድሽ ስብስበሽ ለበይ ልታጠግቢ
ኤሊዎች ቀደሙሽ በማያበር ክንፍ ስትርገበገቢ::



# ጫፍ አልባ ቁልቁለት

የያዙትን ይዞ ካልተንጠላጠሉ
ወደ ላይ ካላሉ
ወ
ደ
ታ
ች

እ
ያ
ዩ
መውደቂያን ካሰሉ
ከውድቀት ዳርዳሩ ከተንደረደሩ
መውደቅ ከጀመሩ
ውድቀት ጫፍ የለውም
ሜዳው ቁልቁለት ነው ውድቀት ዳር የለውም
በውድቀት ላይ ውድቀት እየተያያዘ እየተዋዋለ
ከውድቀትም በታች ሌላ ውድቀት አለ::



http://ethzare.wordpress.com

## ባዶ አርጊኝ

ከንፈርሽን ልጉረስው ላ'ንዴ ከንፈሬን ግመጪው ላ'ፍታ::
በአቶን እስትንፋስሽ ቅጥለት ይትነን የወስጤ አንድምታ::
የቆመው ኩሬ እምነቴ
የወየበው ፍልስፍናዬ
የወረዛው እኔነቴ - - ይድረቅ እንግዴህ ልጣድ፤
አሙቂኝ አንቀልቅይኝ በይ አንድጅኝ በጭንሽ ነዲድ::
አዳውሪኝ ይበጥበጥ ውስጤ፤
ብቀይ ባህር-  ሽሽ ላይ ተጫወች በልቤ ካርታ፤
ሠውሪኝ በገነትሽ ሥር ባዶ አርጊኝ እስኪ ላ'ንዳፍታ::
በዛብኝ እኮ እግዚኦታ!
ይኸው ሶስት ሺ ሃሌታ፤
ይኸው ሶስት ሺ ኡኡታ፤
ጥበብ መቀነትሽን ፍቺ አስረሽኝ እስቲ ላ'ንዳፍታ፤
በእንዲት የፍቅር
ጠ
ብ
ታ
::





## ስርዶ

ድርቀቱን - - - ጉንቁሎ
- - ሳይተክሉት - - - በቃቅሎ
ፅድቀቱን ሲከሰል - - - ይብሰቱን — መንግሎ
አረንጓዴ 'ሚሆን - - - ሲጫኑት — ሥር-ሰዶ
ወደ ሥር - የሚያድግ - - - ከላይ ሸክሙ ከብዶ
በተጫኑት ቁጥር በታረቁበት ልክ - - -
ሥሩ 'ሚለመልም- - በሥራ ሥር እጁ - - መሬቱን ጨምድዶ
ድንጋዩን - - ፈጉ- ቅሎ ቢጫነቱን - ጥሎ
ሲቆርጡት ጎንቁሎ - - - ሲጫኑት ሥር ሰዶ
ቀዩን ቀጥኖ - 'ሚያብብ - - ሸለፈቱን ቀዶ
ስርዶ እኮ - ጀገና ነው
ጀግና እኮ - ነው ስርዶ::



http://ethzare.wordpress.com

## ከራስም ሲታነስ

የግዙፎች ጥላ - ሲያጠላ
አልፍ ነጭ ጥላ - ጥቁር ጥላ::
ከፀሐይ ብርሃን - ሲያጣላ
ከመወየብ ዛፎቹ ስር
ከ...ሥ...ር
ከራስም ከማነስ እኮ
ታኮ
ተጠምጥሞ ወጥቶ በመደግደግ
በጥግ
መሆንም እኮ ደግ
እንደ ሐረግ::
ከብርሃን አብሮ ተቃምሶ
የራስ መቁነን ለመፈለግ
ከመዋየብ ከመጠውለግ
አዛፉ ሥር
አዛፉ ጥግ
ተጠምጥሞም ተጠማዞም
ከላይ ወጥቶ ለመጠገግ::
መሆንም እኮ ደግ
እንደ ሐረግ::



## ድፍርስርሱ ደሜ

አንቺስ አቴ በየወሩ
ሲያጥጥሽ ፍሬ ዘሩ
ያበጠ ማህፀንሽ ግድግዳው
ደምሽ የወጣጠረው
ቀይ ስጋሻሽ ቀይ አንግዳው
ቀይ አበባሽ ቀይ ፍሬው
አበቅቴሽን ያልዘነጋው
የወር ቁጣሽ ሲወጋጋው
የጠወለገው በድርቅሽ  አቶንሽ ያንቀለቀለው
ነግሎ ይወጣልሻል አጠትሽ ሲመነግለው::
ይብላኝ ለኔ ይብላኝ ከቶ
ስቃጠል ለምኖረው ድፍርስርሱ ደሜ መውጫ አጥቶ::



http://ethzare.wordpress.com

## ሰሞነኛ

በሌለ ቅዳሴ ሰሞነኛ በዝቶ ስንዴ እንዲወረዛ
እንደ ዘኬ ቆሎ ዝና እየተነዛ
ትናንት የጉድ ተብሎ ለዛሬ ጠነዛ
ማታ ተድመንምኖ ጧት ሆነብን ጤዛ::
ፅዋ እንደሚረከብ ያቦ ባለተራ
እንዳፈረሰ ቂስ የፅጌ ደብተራ
ስም ሰሞነኛ ነው ገኖ 'ሚሆን ተራ::



## ሰይጣን የታደለው

ሰይጣን የታደለው!
ሱሪው አያልቅበት፤ እህል አይቸግረው::
- - - -አይበርደው፤ አይሞቀው::
ሰይጣን የታደለው!
- - - ቀድሞ ቁርጥ ያወቀው
- - - እፀድቅ - እኩነን ሲል የማይጨነቀው
ሰይጣን የታደለው!
- - - ልጁ እያለቅስበት፤ ሚስቱ ልፍታ አትለው
ሰይጣን የታደለው!
- - - ሱሱ 'ማይደቁሰው
- - - ጎጆ 'ማይቀልሰው
- - - አፈቀርኩ ብሎ
- - - እንገት ማይደፋው
- - - ወሲብ ቅንዝርና ቂም ማያዳፋው
- - - የማያርስ የማይጎርስ የማይጎለጉለው
ሰይጣን የታደለው!
- - - የስልጣኔ አባት
- - - መፈንቅለ መንግሥት
- - - ቀድሞ ያካሄደው
ከሰው ልጅም በላይ፣ ፈጣሪን የሚያውቀው
የፈጣሪን ምስጢር፣ አክስሎ የሞቀው
ባለውለታችን፤ ሊቁ መልአክ ሰይጣን፣ ከበለስ ጀምሮ
የተፈጥሮን ምስጢር፤ ያምላክን ቋጠሮ
ለሰው አቀብሎ፤ ለሰው አንቆርቁሮ
ፈትኖ ፈታትኖ፣
ቀድሞ ተፈታትኖ፣
ሰውን ሰው ያረገው
ግልፁ ደግ መልአክ ሰይጣን የታደለው!
ጥርቅምቅሞሽ እምነት ተደፋ! ተወጋ! ወደ ጥልቁ ውረድ!
- - - ሲለው የማይፈራዉ



http://ethzare.wordpress.com

- - - እኔ ላይ ተባሮ እሷ ላይ 'ሚሰፍረው
- - - ሙስሊም ክርስቲያኑ - ጴንጤ ኦርቶዶክሱ
- - - ካቶሊክ - - -ዊትነሱ - ምዕመን መናፍቁ
- - - ባለዛር ጠንቋዩ - - ድፍን ቅሉ ሲቁ
እስወጣሁት ሲለው ምንም የማይመስለው
ሳጥናኤል ታጋሹ ሰይጣን የታደለው
ሳጥናኤል ሉሲፈር ፀሎት እያደቀው ውዳሴ እያደምቀው
ጨለማ እይዘፍቀው ገነት እትናፍቀው::
ሳጥናኤል ሉሲፈር ፍቅር የራበውን
ከልቤ ጠሊቅ ሥር ምናለ ብወደዉ
ጠላቴ ከሆነ - - ሰይጣን ወዳጂ ነው::
እስኪ በዚህች እንኳ ታላቁን ልብለጠው
ልጁ ሲያስተምረን - ጠላቶቻችሁን ውደዱ ብሎ ነው::
ምነዋ ይህች ቃል ለ'ሱም የማትሰራው?
መቂያቂያም በቂም ልክ ቂሙን ቢደብቀው
ምነው የእሱን ሥራ የማይታረቀው?
ለሰው ልጅ ተሰቅሎ እጥፍ ለበደለው
ምነዋ ወዳጁን ይቅር ይብቃ ቢለው!?

(ለክርስቶስ ሰምራ፤ ወለዘይገርም ፍልስፍና ዘፎገራ)



# ተመየጢ ፈላሲት

ይድረስ ለፈላሻዋ- እነሆ እኔ ሐበሻው ነኝ
ቅድመ ፍልስት- ቅድመ ክህደት ከፍቅርሽ ገፊት ያቀመስሽኝ::
ፈላሻዋ ፍቅሬ ጌጤ የእምዬ ልጅ የእናቴ
በውነኑ ልብሽ ቆርጦ ከዷታል- እማማ ኢትዮጵያን በሞቴ?
በለጋ ልቤ ያጠበቅሽው የፍቅር ፈትልሽ ቁርኝቱ
ጠብቆብኝ የፍቅርሽ - ፍቅሬ ክረቱ
ደግመሽ በፈለስሽበት ምድር- እስራኤልን በመላ እሰስኩ::
"እመሐልኩክን" ብዬ የኢየሩሳሌምን ቆነጃጅት ጠየኩ::
ቴልአቢብ- ጎልጎታ ሳስፈልግሽ ስፈልግ ኖርኩ::
በናዝሬትም-በገሊላም-ፈልጌ አስፈልጌሽ ነበር:
በኢዝራኤል ሸለቆ አድባር- በሞርያም ተራራ ሥር
በዶር ሱልጣን በር ሁሉ ፈልጌ አስፈልጌሽ ነበር::
ግን እስኪ ልጠይቅሽ ያጣሁሽ ፈላሻዋ ፍቅሬ
ድህነት ኢዘለአለማዊ መሆኑ አልገባሽም እስከዛሬ?
ክደሽ የተውሽት ምድር- እምዬ ኢትዮጵያም
ደሀ አሮጊት ብትሆን እንጂ- በእናትነት አትታማም::
ጥበበኛ እጅሽ ይመስክር - ስንዴዋን ለብርሃንታሽ የጋገረው
አለቷን ለምኩራብሽ የፈለጠው - ዋልካዋን ለሸክላሽ የቆፈረው
እስኪ ከናዝሬት- ገሊላ በተመላለሰው ጌታ - እንዴ ልጠይቅሽ ፍቀጂ?
ነፍስሽ ከላይ ከራማ
ስጋሽም ከእማማ ኢትዮጵያ አውድማ የተቦካ እንጂ
እስኪ ስለ እውነት መስክሪ - መሬቷን የሳምሽት እስራኤል
ሆነችልሽ እናት አገር?
ያቺ እማማ ያለበሰችሽን ቀሚስ ያቃጠልሽባት ከነዓን
የምታፈሰው ደም ነው ማር?
ያንቺም ቢሆን ያ ያፈቀርኩት ገላሽ ጥቁሩ
የፍጥረት መቅድምሽ ሥሩ - ጥቁር አይደል ፍሬ ዘሩ?
እስኪ በፈጨሽው ጥቁር አፈር - በቀዳሽው ጥር ምንጯ ማይ
ሥጋዬ የተከመረው እጥንቴ የለመለመው ከእማማ ኢትዮጵያ ጤፍ
ዳጉሳ አይደለም በይ?
እንደ ጣና ሳቢላ በረሽ የሰፈርሽባት ከነአን



http://ethzare.wordpress.com

መቼም ጊዜ ደግ ነው ያደረገችውን ሰማን::
ተንቆረቆረ እሉ ደምሽ ቀድታ ፈትሻ ደፋችው
የእኔ እይደለሽም አለችሽ- ይኸው ቁርጡን እወቅሽው::
አንቺ ፍቅሬ ፈላሻዋ መቼም እናትሽ ኢትዮጵያ
ከርዛት ርሃቧ በቀር ላሳር ነው መቼም ላሳር
እናትነት ከሷ ወዲያ
የግላንግሉ መጠጊያ- እናትነቷስ የጉድ ነው ኢትዮጵያ
ለእምነትሽ - ምኩራቧን ለፍቅርሽ ወጣቷን ሰጥታ -
እኔን ልጇን ለግላሽ
እናታለም ኢትዮጵያ ከእላት ከቶ ምን ነሳችሽ?
ነይ ተመለሽ ስሞትልሽ::



## ዝረፍ ዝረፍ አለኝ

ሽርክተው ሆዱ ላይ
ይጎልጎል እንጆቱ ህብር ቅኔነቱ
ይበጥበጥ ሃሞቱ::
ፊኛውን ሸንትረው
ይንቆርቆር በሆዱ ምስጢር ውል እንቀፁ
የማያልቅ ሽንቱ::
ባዶነቱን ፈትሸ ገቢር ተገብሮውን ከሱሪ ከኮቱ::
ማንደርደሪያው ድረስ ይሩጥ እስከ ቤቱ::
ያንተ ነው የኪሱ ያንተ ነው ጥሪቱ::
ከምስጢሩ ስበር ከጉልጥምቱ መቅኔ፤
ዝረፍ ዝረፍ አለኝ
ንጠቅ ንጠቅ አለኝ የየኔታን ቅኔ::



http://ethzare.wordpress.com

## ተላለፉ ሲለን

ከመረዋው ውግረት  ከቃጭሉ ዋይታ አኩል ብንሰማም
በአንድ ደወል ድምፅ  ግለ ህሊናችን አንድ ላይ ቢደቃም
ተላለፉ ሲለን ፊትና ኋላ እንጂ አኩል አንነቃም::



## እንጋፋው ሱሪዬ

አባቴ አንድ ሱሪ አለው - ጥንት አባቱ ያወረሰው
ጠቦት ጠባቦት ያ'ኖረው::
«ልበሰው» አለኝ ሱሪውን - ብለብሰው ሰፋኝ- ሰፋፋኝ::
በሱሪው ውስጥ ቅማል የሆንኩ ያህል ሰፋኝ
ምዕት ጊዜ አስጠበብኩት - - ምዕት ጊዜ ሱሪው ሰፋኝ::
እልፍ ጊዜ ባስጠብበው - - እልፍ ጊዜ  ጠባበበኝ
ለሱሪው ግመል ብሆንም እየጠበበኝ ለበስኩት - - -
ሱሪዬ ለብሶኝ ታጠኩት::
መቀመጫዬ ላይ ላ'ሳር ሱሪዬ በታች ፈነዳ
ወሽመጥ አስገባሁለት መጣፊያው አገባኝ ዕዳ::
ያ'ባቴን ሱሪ አወለኩት
እኔም ለልጄ አስቀመጥኩት::



http://ethzare.wordpress.com

# አብረን ብንተኛ

ና- - - አብረን እንቆፍር አብረን እንማስን
ና- - - አብረን እንዝራ አብረን እንበትን
ና- - - አብረን እንተኛ እንጋራ አንድ አልጋ
ጀንበሯን ቀስቅሰን አንድ ሌት እናንጋ
አብረን ብንተኛ መደብ ባንለያይም
የራሴን ህልም እንጂ ያንተን ህልም አላይም።



# መንገደ ምርቃና

መሄድ ከተቻለ ሂዱ ሌላ እስሱ ከወዲያኛው አለም
ምጠቁ ጥለቁ ይቅናችሁ ግድ የለም።
ምጠቁ ጥለቁ በጉም ሃሳብ ሕዋ በምርቅንቅን ዓለም።
. . . ግን. . .
ያክር ሲበጠስ
ሲከጅል መመለስ
ምርቃናው ሲሰበር
እውነት ሲበረበር - -
ማንነት ሲቀለም
በፍኖተ ቅዠት በምርቅንቅን አለም
ወሳጅ መንገድ እንጂ መሳሽ መንገድ የለም።



http://ethzare.wordpress.com

## አመክንዮ

ለምን ፈጠረኝ?ትላለህ!
ለምን፤ሞታለሁ?ትላለህ
ዝም ብለህ መኖርክን ትተህ
ዝም ብለህ መሞትክን ትተህ
ለምን ኖርኩ? ለምን ሞትኩ?
እንዴት? አያለ
ላምጭው ለወሳጁ እንጋጠ
ሕሊናህ ለምን ማለለ?
በመኖር ያለመኖር ጫፍ
አመክንዮ ቀድሞስ መች አለ!?

ἀ ἀ ἀ





## ፈሶሎጂ

አሰይ! ፈሳሁ!
ሐሸ! ፈሳሁ!
በቃ! ፈሳሁ!
እስተንፋሽ ቦታ ሲጠፋ ለካስ ፈስም መድኃኒት ነው::
የላይኛው ሲክለከል ልሳን ሳንቃው ሲከስም
ለካስ እንዲህ መድኃኒት ነው በታችኛው መተንፈስም::
የሆድ ብሶት ጉርምርምታ - የህሊና እጦጥ እምቢልታ
ትንቅንቅ ውስጤ ሲመታ - እፍ ሲከረቸም በቃታ
ምናለ በታች ብፈታ!?
በፈስ አብዮት ድምታ - የማንስ አገር ተፈታ?
ወገኔ ባክህ ተጠየቅ - ፈስ ነፃ ፈቃድ ነው?
ወይስ የሽንት መንቆርቆር ማጀቢያ የፏፏቴው ሙዚቃ ነው?
የላይኛው ሲክለክል ምናለ ትንሽ ብንፈታ
ባሕር ማዶ እኮ ወገኔ እፍ ተከፋፍቶ ተገላ
እግር ተነስቶ ተፈሳ::
እምቁ ተጠርንቁ አልሞትም እኔስ እጨስዋለሁ!
ድርግም! አድርጌ እፈሳለሁ
ሆዴ እስኪከሳ ድረስ ድብን! አድርጌ እፈሳለሁ::
ሰው በሌላም ይዋረዳል ለመዋረዱም ግዴለም
ፈስ የያዘን ማዳበሪያ እንጂ የቃየን መስዋዕት አይደለም::
ውጊያውን እንጀት ተንከሶ አጅሬ ቁልቁል ሲረግጠው
መቋጠሪያዬ ሽምቀቁን ክዳር ዕዳር ሲያጠብቀው
እንደ ማታ ጎለል ሽብሸቦ በጅማት መቀነትነት ሽንሽኑን ሲጠረንቀው
እንደ ሌጊዎን ሽብዳ ከላይ እታች ሲያጣድፈው
ሆዴን ሽቅብ ገልብጦ እግሬን ሲያንከረፍፈው
ከርሴ ውስጡ ሲዳምን ከበሮ ሲያክል ተነፍቶ
በልቀት እትልቀት ትግል ደመና ሲዞር እስፋፍቶ



http://ethzare.wordpress.com

የሐምሌን ሰማይ አድርጎት ሆዴ «ድም»... «ግም»... ሲል
ሆዴ የነሐሴ ኩሬ ሆኖ እንዳፈቀረ እንቁራሪት
ቁርር . . . ቁርር . . . ጨርር . . . ቧጭ ሲል
እንደጧት የኪዳን ደወል ከላይ እታች ሳቃጭል
ነጭ ላብ ፊቴን ሲያጠምቀው ሽምቀቅ . . ጭንቅ . ድቅቅ . .
ፉቅቅ . . . ጥምቅ . . . ጥልቅ ድብቅ ሲያደርገኝ
ከንፈሬን ስጨረግደው
ወገን ታዲያ ምናለ ምጤን ብገላገለው?
ድምፁ እንዳይረብሽ አድርጌ ከቋጠሮው በስስ ብፈታው?
መቼም ነፃነት በራበው ምድር «ዘረጥን» ቀድሞም አላውቀው
እንዴው በትንሽ በትንሹ እ-ሱሱሱሱ . . . እንጂ በየደቂቃው
ነገር እንዳይበላሽ ድምፁ ከመ መብረቅ ባርቆ
ያኔ ጥግ ከአድማስ ባሻገር ርቆ
ይሉኝታ ደንበር ተሻግሮ ሀፍረት በቁም ሲረታ
አቤት ያለው የደስደስ አቤት ያለው እፎይታ
የታችኛው ወናፍ ሽምቀቅ ቋጠሮ ውሉ ሲፈታ
አቤት ያለው የደስደስ አቤት ያለው እፎይታ!!
ወገን ታዲያ ምናለ
ያበጠ ጥቁር ሆድ ሁላ ከዚህች ምድረ አፍሪካ
የተነፋ ቀበተት ሁላ ከዚህች ምድረ እንካ ለእንካ
በእከከኝ ልክክህ ታክቲክ ባጉርሰኝ ላጉርስህ ዳካ
በሆድ አብዮት ገፈጠጥ የተነፋ ክርስ ሁላ በተቦካ ባልተቦካ
ወይም በሆድ አብዮት «ሆዱ ካገሩ የሰፋ»
«መድኃኔአለም ያጥብልንና» ሆዱ ካገሩ ሰፍቶበት
የጎረቤት ወሰን የገፋ
ወይም . . . በብግነት ድማሚት ሆዱ
ጥልቀት ላዕሉ የተነካ
በእከከኝ ልክክህ ታክቲክ ባጉርሰኝ ላጉርስህ ዳካ
በሆድ አብዮት ገፈጠጥ የተነፋ ክርስ ሁላ በተቦካ ባልተቦካ
ወይም በሆድ አብዮት «ሆዱ ካገሩ የሰፋ»
«መድኃኔአለም ያጥብልንና» ሆዱ ካገሩ ሰፍቶበት
የጎረቤት ወሰን የገፋ
ወይም . . . በብግነት ድማሚት ሆዱ
ጥልቀት ላዕሉ የተነካ
ምናለበት ቢተነፍስ በእሱሱሱ . . . ድምፅ እየለካ::
የላይኛው በር ሲዘጋ
በታችኛው መተንፈስም መድኃኒት ነው እቴ-ለካ!!



ሐሹ! ፈሳሁ
አሰይ! ፈሳሁ
አራስ ብሎ ሚጠይቀኝ እንደማይኖር አስቀድሜ አውቀዋለሁ::
መቸም በሀገራችን ትውፊት ልማድ እስከ ዛሬ እንደማውቀው
ለፈስ አራስ መጠየቂያ ሳቅ ወንቀት ደብልቅ ነው::
. . . . ግን እኮ . . . .
ቋጠሮ ውሉ ጠብቆበት በሩፋኤል ፀሎት ላማጠው
ከጭንጋፍ ልጅ ልደት ይልቅ ወደል ፈስ እኮ ግልግል ነው::
የከንቱ ልጅ ምጥንና የፈስ ምጥን ሚለያቸው
ከንቱ ልጅ ወደውጭ ቁልቁል ፈስ ወደ ውስጥ መማጡ ነው::
ፈስ ማለት እኮ ወገኔ
በፈሶሎጂ ትንታኔ
ለእያ አዝብጤ መንገድ አቅኚው
የመጥምቁ ተምሳሌት ነው::
ፈስ ማለት እኮ ወገኔ
በፈሶሎጂ ትንታኔ
ክልሂቅ እስከደቂቅ በህቡዕ የሚያብላላው
ለዘመናት ያልተጠና ኑክሊየር ኢነርጂ እኮ ነው::
በፈሶሎጂ ትንታኔ
ለአህያ መደንግፀ-ጅብ
ለውሻ-የጨኸቱ አጀብ
የህልውናው ቃጭል ነው
ሌሊት አዳሜ ሲያሸልብ::
ሐሹ ! ፈሳሁ
አሰይ ! ፈሳሁ
እንኳን! ፈሳሁ::
አስተንፋሽ ገደል ሲጠፋ ለካስ ፈስም መድኃኒት ነው::
የላይኛው ሲከለከል ልሳን ሳንቃው ሲከስም
ለካስ እንዲህ መድኃኒት ነው በታችኛው መተንፈስም::
የሆድ ብሶት ጉርምርምታ - የህሊና እበጥ እምቢልታ
ትንቅንቅ ውስጤ ሲመታ - ልሳን ሲቆለፍ በቃታ
ምናለ በታች ብፈታ!?
በፈስ አብዮት ድምታ የማንስ አገር ተፈታ? ÷
መቼም ነፃነት በጠማው ምድር «ዘረጥን» ቀድሞም አለውቀው
እንዴው በትንሽ በትንሹ ምናለ ፈሴን ብለቀው?



http://ethzare.wordpress.com

## ኪርያላይሶን

ታኦስ ናይናይ ኪርያላይሶን
ትስቡጣ ናይናይ ኪርያላይሶን
አዶኒ ናይ ናይ
ኢያልኮ ቆሜ ስፀልይ
ፍላጎቴን ቃሏን ገድፌ
ጥያቄ እንቡጧን ቀጥፌ
ኡኡታ አይኖቿን ጠቅቼ
በአርምሞ ቀጭን መርፌ
መሻቷን ውስጤ ቆልፌ ተማፅኖዋን ገርፌ
በግለቷ ውኃ ከልሼ
ቅዠቃዤዋን አምሼ
ውስጤን ራሴን የወጋሁ
በኪርያላይሶን እንካሴ
«እምባገነን» የምል ሌላውን
እምባገነን ነኝ የራሴ።



## ምነው እምና በሞትኩ

እከከከከከ . . .! እህህህህ. . !
. . . እበስኩ . . ገበርኩ . .
ምነው እምና በሞትኩ!
ብጣቂ መሬቴ ወስደው ሳይተኙባት!
መቃብሬን ሠርቀው ሳይቀበሩባት!
እህህህህ. . .! እበስኩ ገበርኩ!
ምነው እምና በሞትኩ!

(ኦ ሔዋን መሬት አንቲ)



http://ethzare.wordpress.com

# እንዲሞቀው በድኔ

ጥጤ ዛሬ ጥጤ
ጥ...ቋ...ሩ...ን... ዘርቼ ያበቀልኩሽ ጥጤ
ውሃ የደፋልሽ ያረመሽ ጣቴ
ሊያባዝትሽ መጣ ለባዳ አከላቴ::
መሆንሽን ቢያውቅማ የውስጥ ከፈኑ
ቢያወፍርሽ እንጂ እንዲሞቀው በድኑ
መች ያሳሳሽ ነበር ያኔ በቀጭኑ::



# ይቀረኛል

ጉጆዬን ልሠራ ሐረግ ስመዝ ኖሬ
ማገር ስቆርጥላት የትም ዞሬ ዞሬ
ራሴን ልችል ነው እያልኩ ከችግር
ቆሳ - ደጋ ስግር
ለካስ ይቀረኛል አብሮ የሚያማግር
ውሃ የሚያቃጥን ተስፋ የሚያጋግር::



http://ethzare.wordpress.com

## ሲያጋጥም

ልቤ በግኖ ነዶ ራሴን በፎከትትኩት
ሌላኛ ጠላቴን ቅማሴን ገደልኩት::



## ልኬታ

እናቶቻችሁን ለኩ - - እኔም እናቴን ልለካ::
የፍጥርጥሬ ውል ሥሩ ዘረመሌ ውስጧ ሲቦካ
«እም» ብላ አግተምትማ
እህ ብላ ንጣኛለች ለካ::
- - -ለካ እንዲህ ነው ለካ- - -
ገንፍዬ ያቆሸሸኳትን አረፋ በፍትወቷ አቦል በረካ
የግብረ ሥጋዋን ጨምገጊት የቅንዝርዝር ምንዝሯን ሳንካ
«ልጄ» አለች እንጂ ለምደባት ህጋዊ ውርጃዋ ነኝ ለካ::
ትውልድ እናትክን አስለካ
ትውልድ አባትክን ተለካ
ፍጡር ነኝ ያለ ሰብአዊ ከእናት ከአባቱ ሲከካ
ስንቱ ነው የተወለደ ስንቱ ተጠርቶ ነው የፈካ?



http://ethzare.wordpress.com

## ሳይቀርቡ ቆርቦ

ማወቅስ ቀድሞ ነበረ ቀስ በቀስ
ቀርቦ ብልልቶቹን መቃመስ።
በፍቅር ልቡን አብሮ ሆድ ምጣድ ቀጨን ማባለት
በባረ ውስጡ መቀባት።
ሀሳብ ቁጢቱን መቋጨት
ማወቅስ ቀድም ነበረ እውቀት
- - - አሁን ግን- - - -
ከንቱ ወበከንቱ ነው ቂስ ቆሞሱን መወቃቀስ።
ከንቱ ወበከንቱ ነው ሳይቀርቡ ቆርቦ ማለቃቀስ
መቼስ የላይኛው ካልቸረ ቁርኙቱ የማይበጠስ
«እጭ አማጩ» በምን ያውቃል ሰው በማንኪያ አይቀመስ።

ጅ ጅ ጅ



## ሰቆቃወ ቂል

............................................እናም
መውደዴን ባልነግርሽ ሆኜ ጠረቀናም
እኔ በአንቺ አልቀናም።
ይሥረግረግ ያንቺ ሠርግ ይደስደስ ያንቺ ዳስ።
ዳስሽ ተደስድሶ ባልሽ ተመርቆ
ልቁጠር እንደ ዘመድ ሰባራ ብርጭቆ።
አልፍ አእላፍ ውሻ በአጥንት ሲጣላ
ከጓሮአችሁ ቆሜ ይሸተተኝ እተላ።
ጥንብ አንሳ ይከሳብኝ ከሥጋችሁ ስርቆ።
ይሸተተኝ በጓሮ ፈርሱ ከጥንብ ልቆ።
ሳልፍ በደጃቸው በፈረሰው ዳስሽ
«ና ቅራሪ ጠጣ» ይበሉኝ እናትሽ።
ክሳምንት በኋላ ከተደፋ እተላ
ሚዜው ዕቃ ረስቶ ጠፍቶ ተላላኪ
ይላኩኝ እናትሽ ልበል «ሰላም ለኪ»።
የሌላ መሆንሽ ፍፁም ተረጋግጦ
ልቤ በደም ጠልቆ ጨቅይቶ በሽቅጦ
ኩስምኜ ኩስምኜ እንደ አባቴ ጥጃ
ከጓሮሽ ቀብረውኝ ይብቀልብኝ ሙጃ።
ለቂል አይኔ አርጥባን የልቤ ውስጥ ዳጎን
ነይ ላውስሽ ጥፍሬን እክኪበት ባልሽን።

ጅ ጅ ጅ



http://ethzare.wordpress.com

# ሀሳሲ ፈላሲ

የጥበብ ቤት ጠፍቶኝ አሰስኩ ሜዳ ሰርጡን
ለፌ ወለፌ እያልኩ የብብቴን ሳላይ የቆጡን የባጡን
በስንቅ አልባ ፍልሰት ያጣሁት ሳስሰው
ለካስ ጥጌ ኖሯል ቀድሞ ሲቀልሰው።



# ዝግመተ ለውጥ

ከማህፀነ ዱድያሴብ የሰው ልጅ ቀድሞ ሲፈጠር
በልሙጥ ጥፍጥፍ ፊቱ ላይ አፍንጫ የለውም ነበር።
ከሰመመኑ ሲነቃ እያትና በገነቱ በር
ከአጥንቱ ገመገም አድባር
የሰረቀችውን ጀምበር
በፍቅሯ ጨረር ስትወጋጋው ዕንባውን አንቀረቀረ።
በእንባው ድንገተኛ ጎርፍ ልሙጥ ፊቱን ሸረሸረ፤
ፀሐይዋ ስትጠልቅበት ወደ ምዕራቧ በረረ፤
በእንባው ፊቱን ቆፈረ፤
በሁለቱ አይኖቹ እንባ ሁለት ሸለቆ ፈጠረ፤
በሁለቱ ሸለቆ መሀል ትንሽ ተራራ ቆለለ፤
ዕንባውን የሚምግበት ሁለት ቀዳዳ ነደለ፤
ስለተራራው ስያሜ ማንም ምንም አላለ፤
አስቀድሞ እሱ ራሱ «አፍንጫ» ስላስባለ።



http://ethzare.wordpress.com

## የጥጃ ምስል

አወይ ላምዋ
ተ ላ ላ ዋ
አርግዛ አሳት - አምጣ አሳት
ወልዳ በዱር - አዛፉ ስር
ጆማት ነገር ውትርትር
ቢሞትባት ሳትጠግበው ቆዳውን ገፈው አውጥተው
ሥጋውን በገለባ ሰግተው አጥንቱን በእንጨት አጥንተው
ታ ም ቆ - ተ ጠ ር ን ቆ
ምስለ ጥጃ ሕይወት አልባ
አፅመ እንጨት ወገለባ
ከጡትዋ ስር ተሸጉጦ
ላያስወርድ ልጎ ንጦ
አወይ ላምዋ ተላላዋ
አለ መስሏት እምቦሳዋ
ከሞት ማደም ፍቅር ቻሪ ለሙት ቁርበት::
ከወተትዋ ኽርንቅ ኽርንቅ
አላቢዋም ፍንድቅ ፍንድቅ
ሲያታልላት ቂቁይ ዋሾ
በኩርማኑ ጨው መላሾ
አይ ላምነት የዋህነት እናትነት
ፍቅረ እናት እስከ ሲኦል እስከ ገነት::
ቁረንጮ ላሽ ላምነት ላሽ
ቆዳ ነካሽ::
ሳታውቅ እውነት
ነክሳ ቁርበት
ከረመች ስትታለል ስትታለብ
እንድታወርድ ለወተትዋ ስትቀለብ
ግን እኮ ብትሰረስረው
ከደረቀው ጅራቱ ስር ብትፈታታው
ትበላ ነበር ከጭዱ
ከሥጋው ከገለባው ከጉዱ:



## መቅደሴን

መቅደሴ ነሽ አንቺ፣ የዞትር አጣኘሽ፣ ካህንሽ ነኝ እኔ::
በመንበርሽ ዙሪያ እየወዘወዘ - - ብወረብ በቅኔ.......
ማነው ያጠነብኝ? ጠረንሽ አይደለም አይደለም ዕጣኔ::



http://ethzare.wordpress.com

## ይበለኝ

የኔ ገብስ ዛላ
«ማማ» ሳልሰራልሽ «ወንጭፌ» ሳይሰላ
«ወፍሽን» «እር». . ሳልል «ማሳየን» ሳላጥረው
ኑሮዬን ሳሰላ
ሳያሽሽ «መዳፌ» ታንቀህ ክረም ሲለኝ
ምርቅሽን ሳልከላ እፍ ሳልል ቅሜሽ
ይሄው እስከ ዛሬ ከትናጋዬ ነሽ::

ፚ ፚ ፚ



## ሕልም እልም

ነቃሁ ፤ ባነንኩ ፤ ህልሜን ነገርኳቸው::
«ህልም እልም» በል አሉኝ ፤ መፍታት ሲሳናቸው::
ከእልፍ እንቅልፋሞች ፤ ከስንት እልማጭ መሀል
- - - - ጉርብጥብጥ ጎዝጉዤ
በነቃሁበት ልክ ፤መልሼ ተጋደምኩ፤
ደግሞ ፍቹን ላልም ፤ ህልም አለሜን አሰስኩ::

ፚ ፚ ፚ



http://ethzare.wordpress.com

# እዕምራ ለሒዌዋን

ሳይበርድሽ ስደርብ
ሳይሞቅሽ ሳራግብ
እባብ ስሆን ርግብ
ስማስን የኖርኩት
የተንከራተትኩት
«ህትምት ድንግል ነኝ ማንም ያላቀፈኝ» በማለትሽ ነበር::
ስጠብቅሽ የኖርኩ ስሸኝሽ እስከበር
. . . . . እኔም . . . . .
ያኔ ስጠጋሽ ስትጣጊኝ በእንቆቆ እንደማይሽር እቡይ ኮሶ
ስንማማል በአመብርሃን ስንገዘት በአምላክ ጠሶ
እንደ አንቺ የሥጋ ድር ባይኖረኝም የደም አውታር
ውሳጤዬ ድንግል ነበር::
. . . እናም . . .
በዘመን ላይ ዘመን ደርቶ
የሠርጋችን ችቦ በርቶ
ጫጉላ ገባን ልንተያይ
በሒዌን ዓይን ልትወጋጊኝ በአዳም ዓይኔ ገላሽን ላይ::
ድምፁን ሰማን «እእምራ ለሒዌን» ን
ስትገሠሥ ድንግልና
ያች ለቅሶ ጥዑም ቃና
ነጠላ ድበፅ እልፍ ዜማ
እስከ ገነት እስከ ራማ


አዲስ ምድር አዲስ ሰማይ
ልናንጋጥጥ ሽቅብ ልናይ
ሲደረመስ አዲስ ገደል አዛኝ ወጊ ጣፋጭ ቁስል
ትኩስ እንባ ወላፈን ጠል ጥፍር ሲሾል ወስፌ ሲግል
እኒያ እናትሽ ያባረሩኝ የዘጉብኝ
ሲያወድሱኝ ጀግና ሲሉኝ ብር አምባርሽ እንዲሰበር
ለደሙ ጨርቅ ሲቀነቀን ሲደነከር መስሉኝ ነበር:



- - - ሆኖም - - -
በጆሮዬ ተማፀንሽኝ ለዘመናት ከደበቅሽኝ
ሕቡዕ ምስጢር አካፈልሽኝ
«እምጣ ምላጭ ሰንጢ ስጠኝ!
ደም ፍለጋ ጭኔን ቧጠኝ! የደም ጨርቁን ለውስልኝ»
. . . አልሽኝ . . .
እቱ ተይው . . . ውዴ እርሽው ስለ ፍቅሬ ሁሉ መልካም::
ቀድሞም ቢሆን ባንቺ መድማት እኔ አልረካም::
በሥጋ ሥሥ በደም አውታር ንፅህና አይለካም::
ተፍገምግሜ ተጥደፍድፌ
ከሱሪዬ ሰንጢ ልፌ
የራሴን ጭን በጥቻለሁ - - ደምሽን ከኔ ደምቻለሁ
ብር እምባሬን ሰብሬአለሁ የደም ሻሹን ነክሬአለሁ::
እቱ ተይው . . . ውዴ እርሽው ሁሉ መልካም::
ቀድሞም ቢሆን ባንቺ መድማት እኔ አልረካም::
በሥጋ ሥሥ በደም አውታር ንፅህና አይለካም::



http://ethzare.wordpress.com



(ጥቁር የበላይ የሆነባት ብቸኛዋ ሀገር ማኪያቶ ናት።)

## ዕንባ ማኪያቶ

እስከሚዋሀዱ እስኪደባለቁ
ዘላዕሉ ፀላም አርሙን ከላይ ሆኖ
ቡና መቦረቁ
ያ ያልተዋጠለት ፀአዳው ወተቱ
ከታች ሆኖ ሽቅብ ቡናን መጋፋቱ
ብሔረ ማኪያቶ ሀገረ እንቶፈንቶ
ሀገረ ቀረርቶ
እንዳይኖር ሰላሟ ዘለዓለም ተናግቶ
ማንኪያ ፍቁረ ዕድ
ላይ ውጣ ታች ውረድ
ተፋጅተው ሳያልቁ አድርጋቸው ውህድ።



## የግጥም ጅምናዚየም

ቦርጫም ግጥሞች ሁላ እስኪያለክልኩ
ቅርፅ ምስጢራቸው እስኪገባ ልኩ፤
ለሆኑት ቀጫጫ ሰላላ መላላ
አልሚ ምግብ ህብር ቢሰጣቸውና ጎናቸው ቢሞላ፤
ዱብ ዱብ እንዲሉ እንዲቀበቀቡ፤
ለግልበት ብርዳቸው ሰምና ወርቅ ባዝሊን
ቀድመው እንዲቀቡ፤
ግጥም ጅም ታንፆ ምናለ ቢገቡ።



http://ethzare.wordpress.com

# የአፈ ጉባኤው መዶሻ

ይድረስ ለጉልያድ ውላጅ ዳዊት መስለኸኝ ለመረጥኩህ
መዝሙሬን ልትዘምርልኝ ዕንባዬን ልታነባልኝ
እኔነቴን ለወከልኩህ::
እዳሜ በአንተ ደነቀው ዕድሌ በአንተ ጨነቀው
እልፍ እጅ ሲንጨባረር እንቅልፍህን ስትሰልቀው::
ዳሩ ልብ ባልል ነው
ያ ሐዋርያ የለፈፈው
ለሮሜዎች የተጻፈው
ለውጭንቅር አእምሮህ መንደር በግልባጭ እንዲህ ይላል
«መዶሻ የመረጣቸውን ማን ይከሳቸዋል?
የሚያጸድቅ መዶሻ ነው የሚኮንንስ ማን ነው?
. . . . ይልቁንስ . . . . .
ጉልላታችን ያነፀው ካስማ ማገር ያፋቀረው
ወፍጮ ከመጅ የሚወቅረው በአፈ ጉባኤው ቀኝ ያለው
እኛን እኛን የሚወቅረው መዶሻው ነው::»
ያ የነገር ማሳረጊያ
ያ የርዕዮተ ዓለም ማፅደቂያ
ያ የልዩ ሐሳብ መድቂያ
የሚኮንን የሚያፀድቀው
የአፈ-ጉባኤው መዶሻ ነገር ቁጭት የሚያጠብቀው
ምናለ «ንቃ» ብሎ እናትክን ቢበጠርቀው::

(ቢፓርላማ ለሚያንቀላፉ «የሕዝብ እንደራሴዎች»)



## ኩርኩም

አልፍ ኩርኩሞችን
የቀመሱ ራሶች
ዳሳሽ እጆች እንጂ
አይሹም ትራሶች::

1993 ዓ.ም



http://ethzare.wordpress.com

## የገሀነም መዝገብ

አንድ ጠማር አንድ መዝገብ፣ አምልጦ ወድቆ ከሰማይ፣
ወደ ገሀነም የሚገቡ፣ ሰዎችን ዝርዝር የሚያሳይ፣
አነሳሁትና ስበር፣
ከራሴ ስም አስቀድሜ የፈለኩት ያንቺን ነበር።



## ሉልነት? ሉሌነት?

ድንቁም አንድ መንደር
ሉሌነት ነው ትርፉ አንጉል መገደር
ሰሰጠንን ስንል አንድ ጡት ተጣባን
ከመሀል አራዳ
ገዳመ ሉሌነት ለአርምሞ አስገባን
ከእናታችን ጓዳ አስቀረቀረብን
ሳናረጅ መንኩሰን ሳንፆም ቆረብን
አንድ መንደርነት ሉልነት የዋጁን
እንኳን ተጕራብተን በሩቁም አልበጁን!



http://ethzare.wordpress.com

## የትኋን ሽቶ

ለፈንጣጣ ጣጣ
ፈውስ መድኃኒቱ ከመግል ከወጣ
ከትኋንም ሽቶ ማምረት ብንጀምር
ማንም ግድግዳውን አያስረጭም ነበር



## አግቡኝ

እናንተ የቦዘናችሁ
እናንተ የተከዛችሁ
ቁመቀር ወፈት 'ሚሏችሁ
እናንተ ጋለሞታች ደናግል ጋለሞታዎች
ገደላችሁ ሥራ ፈቶ ከሚዞሩት አሞራዎች
ኑ . . . እኔ ልድፈነው ባለኝ በተሰጠኝ ዕቃ
መቼስ ጋብቻ ስሜት እንጂ ማደባለቅ አይደል ዕቃ፡፡
አየነው አይደል ስንቱን ድብቅ ስሜቱን ወሽቆ
ተቀራርቦ በፈገግታ ተላልሶ ተሳስቆ
ተጣጥፎ ተፈራርሞ ተፈጣጥሞ ዕቃ ብቻ አደባልቆ
አየነው አይደል እንዴ ሰማኒያ ውሉን በጫጭቆ!
ኑ. . . ባንድ ጥላ እንጠለል
ኑ . . . በአስተሳሰብ እንጋባ ፊርማ ወረቀት አልባ ውል፡፡
እንኳን ለሰባታችሁ
ለአልፍም እበቃለሁ፡፡
አለኝ ጥሩ ማረሻ ሰርዶ የሚነቃቅል
ስርቻ ጉጡን መንግሎ ጭንጫ ላይም የሚያበቅል
ሽጥለሽጥ የሚያጨቀጭቅ ከምድረ በዳ ሚበቅል
እንደአላዛር ሞቶ 'ሚነሳ ስንኩፍ መግነዙን የሚያቀል
አርፍ ስሜቱ ሲነቀነቅ የሚተከል የሚነቀል
ተንጠልጥሎ የሚላጋ አለኝ ጥሩ ማረሻ
የአጦት ዝገት ነጥርቆት እጣ እንጂ ማባበሻ፡፡
ኑ . . . ገደላችሁን ልረሰው ዳዋ አይብቀልበት
መቃብር አይሁንባችሁ ሀፍረትን 'ምትቀብሩበት
በጉራንጉር ጥጋጥጉ ማዕበል አይዝለልበት፡፡
በጭቃ አሮንቃ እገሮችሁ አሪያችሁ አይደንክርበት፡፡
ፍቅር ከቆጠቆጠ ቅናት ካልለመጠጠው
የፍቅር ቡቃያ ጉጡን «የኢቲክስ» አረም ካልዋጠው
እንኳን ለሰባታችሁ ለአልፍም እበቃለሁ፡፡
ሰው መቼም ነፃ ቢወጣ ከደዌ ሕመማት ቁጣ
በመደሰቻችን በኩል በታች ከመጣብን ጣጣ
ሰው መቼም ነፃ ቢወጣ ከሕግ ከምግባር ሰንሰለት
ቅድስና-ምንዝርና ትንሽ ምክንያት ጨምሮበት
እንደ ሰለሞን እንደ ዳዊት ለብዙ በበቃ ነበር
የፍቅር ነበልባሉ ግለት፡፡



http://ethzare.wordpress.com

በሕልመ ሌሊት ቅዠቱ ተፃብኦ ሲያዳክረው
ጀንዲውን አበስብሶ ትራስ ጭኑን ሲያሳቅፈው
ኮርማ መሆን የተመኘን እንግዴህ ምንጣፍ ይቁጠረው
. . . እ . . .
በኮርማ እንቅልፍ ስምጠት መሃል አረፍት እንጂ ግለት የለም
ኮርማ እውኑን ይኖራል እንጂ
ሕልም አለሙን አያቅፍም  መቼም::
ኑ . . .  ጣራዬ ሥር እንጠለል
ኑ . . . በአስተሳሰብ እንጋባ ፊርማ ወረቀት አልባ ውል::
ኑ . . . አግቡኝ ልሁን የጋራ
ሽለቋችሁን ልረሰው የጠበብቃችሁን ጋራ::
የቅናት የግለኝነት የስስት ውላጅ ባይወርሰው
መሠረቱ መሬት ነበር የዚያ የቀደመው ሰው
የቅናት የግለኝነት የስስት ጩቤ ባይምሰው
ሰው እኮ መሬት ነበረ ሁሉም በጋራ የሚያርሰው
በጠበቀው ባጠረው አይደል «መሬት እኮ ላራሹ ነው!!»
ፈጣሪ ቀድሞ ሲፈጥረው ሰው እኮ ድሮም መሬት ነው::
የሰው ልጅ የመሬት ሥሪት ዱድያሌብ ነው ከተባለ
የጋራ ሁዳድ አውጥተን አርሰን ብንዘራው ምናለ?
በአንድ ጋግርታም «ሞኖፓል» ስሜቱ ከስሎ እያደረ
በአንድ ወታሻ ጥላ ስር ሥራ ስሩ ከደደረ
የስሜቱ አበል ገንፍሎ ከሚሆን ዝቃጭ በረካ
ምናለ በሰብሰብ ጉልበት ለአንዲት አፍታ እንኳ ቢረካ?
ሰው አለኝ ማለት ከንቱ!
ደሀ ተሽጦ የማይገዛው ቅቅታም የተለተለው
              ሊዝ ነው እንዴ እንደመሬቱ?
... መቼም...
የራሴ የግሌ ባዩ የሰው ልጅ ብልጠት ሲለካ
በሰለጠነ ቁጥር ቅናት ያጠቃዋል ለካ
ኑ . . .  ጣራዬ ስር እንጠለል
ኑ . . . በአስተሳሰብ እንጋባ ፊርማ ወረቀት አልባ ውል::
ጉድለታችንን እንድፈን ቀዳዳችንን እንዘጋ ባለን በተሰጠን ዕቃ
መቼስ ጋብቻ ስሜትን እንጂ ማቀላቀል አይደል ዕቃ::
ኑ . . . እቴ ... ተድመን እንንቃ
ስሜታችንን እንጂ ማቀላቀል ይቅር ዕቃ::



# ጢም አልባ

ለቅንድብሽ ፀጉር ፀሐይ ሲጠልቅ አይቶ
ከንፈርሽ ሲቀባ እንዳንራብ ለግቶ
የደቂቆች አምላክ አስቦ ለጊዜ
ጢምሽን አያበጠርሽ እንዳታይ አባዜ
ውበትን ሲያድልሽ ሲያደርግሽ ወለባ
አገጭ ብቻ ሰጥቶ አረገሽ ጢም አልባ::



http://ethzare.wordpress.com

## ብርሌ ሲነቃ

ብርጭቆ የዚች ጥቁር አፈር ግኝት
ባሕር ማዶ ስትሻገር
ሆንክ አሉ ማይክሮስኮፕ አጉሊ ነገር፡፡
ከኛ ምድር እስከ ዛሬ - - አለህ ነገር ስንቀዳብህ
ጠጅ ስናንቆረቁር፡፡
«ብርሌ ከነቃ አይሆንም ዕቃ» ብሂሉ
የስንፍና መፈክራችን የጥበብ ጥበት ነው ቅሉ፡፡
ብትነቃ እንኳ አትሆን ዕቃ፤
ስባሪህ ለምን ሲበቃ
ንቃትህስ ማንን ሲያነቃ
ብርጭቆ የስልጣኔውን ምስጢር፡፡
ከኛ መንደር - - እኛ ሀገር - - ከኛ መንቆር
ሁሌ ጠጅ
ማ
ን
ቆ
ር
ቆ
ር

⸎ ⸎ ⸎



## ልናነጋ ተኛን

ጨለማ ሲገዝፍ በቀን እኩይ ድርጊት
ዝንተ ዓለም ሳይናድ የጨለማ ምርጊት
በድሜጥሮስ ኩፋል «ቀን- ጨለማ» እያልን
ልንውል ተነስተን ልናነጋ ተኛን
በድሜጥሮስ ኩፋል
በገማ ጭንቅላት ጨለማ እየቆጠርን
እንደ ወፏ ሞረሽ በማያነጋ ድምፅ ሁሌ እየተብላላን
አንድ ቀን ሳንውል ሦስት ሺ ዓመት ሞላን፡፡

(ለኢትዮጵያ የሦስት ሺህ ዓመት ታሪክ)

⸎ ⸎ ⸎



http://ethzare.wordpress.com

# እያቴ

«ኣከከኝ» ይላሉ ታከው ላይጠረቁ
«ኣቀፈኝ» ይላሉ እንደውሻ አፍንጫ
እየቀዘቀዙ ቆፈን እያጨቁ
እኔን እደንዝዘው ሙቀቴን ሊሞቁ
ደግሞ ብለው ብለው
ደግሞ እንደ ማሊያ
በሞት ዋዜማቸው
ያልበደለች ነፍሴን ይዘዋት ሊከንፉ
«ነፍስ እንለዋወጥ» ብለውኝ አረፉ::

ዻ ዻ ዻ



# ጉባኤ ፍና

በፅባሕ ተንሥኢ ብዕረ እዴዬ መባልና
እስመ ኢየሀልቅ ለነ ቅኔ ዘርዓ ሰብዐ ፍና::

ዻ

እመበለት ብዕሬ
በጠዋት ተነሺ (እንበል ጉንበስ ቀና::)
የሰው ቅኔ መንገድ - ከቶ እያልቅምና፤
(በኔው እረማመድ ባንቺ ጉንበስ ቀና)
(በጠዋት ተነሺ ሳይቀትር እንጓዝ በቅኔ ጉዳና::)

ዻ ዻ ዻ



http://ethzare.wordpress.com

# ኤዲት ይደረግ

በገብርኤል ሰይፍ ገማምሰን
የሰማይን ቅጥር ጥሰን
ኢዮር ራማን አሰሰን
ፅርሐ አርያምን አምሰን
ካለበት ጉራንጉር ደርሰን
«እግዚአብሔር» ቃሉን
ኤዲት አርገነው በመጣን::
ቀድሞስ «እግዚአ-አብ-ሔር» እንጂ
«እግዚአ-ብሔር» መች አጣን::

ጰ ጰ ጰ



# ሚዛኑ

እየተንገለልን- -እየተበጠርን
እየተነፈስን- - እየተነፋንም
አንዱን አሳንሶ አንዱን እየለካ
በራሱ ልኬታ ሲሰፍረን ቢኖርም
ቡኬት ዱቄታችን በቆጥና - ባጡ
ታችና ላይ ወርዶ ተንጋዶ ቢለካም
ሚዛኑ ዕድሜ ልኩን ራሱን አይለካም::

ጰ ጰ ጰ



http://ethzare.wordpress.com

## ከ'ኔ በጥቂቱ

ኣ

ያ መፍጠሪያ ፍጡር ከአማልክት በታች
በጥቂት ባነሰ ተፈጥሮው ሳይረካ
ተፍጨርጭሮ ነበር አምላኩን ሊተካ።
ያ'ሁኑ ፍጡር ግን- - -
ከ'ኔ በጥቂቱ በመብለጡ ረካ።

ኞ ኞ ኞ



## አቤቱ

ሊቀመዝበር የወዝበር አለቃ
ስጠን።
ሊቀስብዕ - የሰው አለቃ
አታምጣ።
ሆዳችን ላይ ተቀምጦ
ጭንቅ- ላታችን ገረጣ።

ኞ ኞ ኞ



http://ethzare.wordpress.com

## ትበጥብህ?

ያች የተለጋች ጥንግ- - የተለጋች አሩር
የተለጋች እንቁር በገና ጫዋታ
እራሴን ስትነድለኝ ላፍታ በጨረፍታ
«እንትፍ» «እንትፍ» ብለው «ትበጥብህ» ሲሉኝ
በግኜ ነበረ በበደል ላይ በደል ያከሉብኝ መስሎኝ
- - - -ለካስ- - - -
ወደውስጤ እንዳላብጥ
በህሊና ቁጣ እቂም ቁስለቱ
መግሉ የሚከስመው
የላይኛው እበጥ ነበር መድኃኒቱ::



## ዘመነ መንሱት

ለዘመነ መንሱት
ለዚህ ጥቁር ቀኔ
መቼ ቦዘንኩ እኔ
ቦዘኔነቴንስ
እ...ደ...ገ...ኛ...ነ...ቴ...ን እጂቶቅርፎልኛል
ከሥራ አስገብቶ ያስወለውለኛል::




http://ethzare.wordpress.com

## ስለት

በስለት ፀንሰውኝ በስለት ወለዱኝ
በስለት አድጌ በስለት አለሁኝ
መጥፊያየም በስለት እንዳይሆን ሰግቼ
ሌላ ስለት ተሳልኩ ጧፍ ሻማ ገዝቼ፡፡





የግብፅም ንጉስ አንዲቱ ሲፓራ
ሁለተኛይቱም ፉሐ የሚባሉትን
የዕብራውያንን አዋላጆች
እንዲህ ብሎ ተናገረ፡-
እናንተ የዕብራውያንን ሴቶች ስታዋልዱ
ለመውለድ እንደ ደረሱ ባያችሁ ጊዜ
ወንድ ቢሆን ግደሉት ሴት ብትሆን ግን
በሕይወት ትኑር፡፡
ዘፀአት 1፡-15

## የወንድ ምጥ

አዋላጅቱ ሲፓራ ቃለ ፈጣሪን ዘንግታ፣ ቃለ ፈርኦንን ከሰማች፣
ፉሐም «ለእልል ዘጠኖ» አድልታ «እልል አስሩን» ካደማች፣
በፈርኦን ጠልሰመ መርገምት በእኩይ ኩፋሌሽ ተማምለው ሲዳዳሩ፣
ወላጆች ሊጨነግፉ «ለሴት እውል» ምጥ ካደሩ
ግሽር ዘረመል እንስቶችሽ ወንድ ማማጥ ካልተማሩ
አዋላጆችሽ እንስት እንጂ ወንድ ውሉድሽን ካልማሩ
ያለ እናቱ ካረገዝኩት ለአድርባይ እንስትሽ ተውላጥ
ወንድ ውሉድሽን «እህ!» ልበል
የውስጤ ሳንቃ ስኪነቃ የማህፀኔ በር እስኪላጥ፡፡
የማህፀንሽ ፍሬ ዘሩ ገለባ እብቁን ለብቆ
ሆድሽ በፍልፈል ገፈት ሽርት ውሃ እርሾሽን እብቆ
ምድርሽ በጭንጋፍ አደፍ ገደልሽ በጭንጋፍ አትብት
ከተሞላ ውሎ አደረ፡፡



http://ethzare.wordpress.com

ወላድ መሳይ ማህፀንሽ ላለማረጥ ሌላ እንቁላል ተበደረ፤
የፈርኦንሽ እዋላጆች ሆዱ ሲገጥ ቅብ ፊታቸው ጠቋቆረ፤
በስደቴ ጨረቃሽ ዓይኑ ደም ቀላ ፀሐይሽ ፊቱ ጠቆረ::
. . . . እዩ እመት እፍሪቃ . . .
ዶሮሽ ተኝቶ እደረ፣ ጴጥሮስሽ አላለቀሰኩም::
የይሁዳሽ ፀፀት ዘግይቶ፣ ይሄው ዋይታዬ አልሰመረም::
ወንጭፌም የራሴን ክንድ እንጂ፣ጎልያድሽን አልሰበረም::
ምጤ ሽብዳ ሆኖ፣ ደንደላም ፀርሽን ካልወጋ፣
ሐሳቡ ወጋገን ሆኖ፣ ጠቋራ ሌትሽ ካልነጋ፣
ምኑ ላይ ነው እመት እፍሪቃ፣ የኔ በሥጋ መገለጥ፣
የሕልውናዬ ዋጋ?
ጥቁር አፈርሽን አቡክቶ፣ በራሱ አምሳል ሲሰራኝ፣
እስትንፋሱን እፍ ብሎ፣ «ሕልው-መዋቲ» ሲያደርገኝ፣
ጎርፌ እንዳልፍ ከሆነ፣ «ሕይወት-ሞት» ... በሚለው ስርጥ፣
ዋጋ ቢስ ነውና ጥንቱን፣ የኔ በሥጋ መገለጥ፣
ሥጋዬን አፈርሽን ውሰጅ፣ እሱም እስትንፋሱን ይዋጥ::
ጆሮሽ አዝነ እምላክ ሆኖ ቤተንግሥ ካልሽው ኩይሳሽ የምስጥ
ሹክሹክታን ቢያደምጥም
ለኔ ግን ታምቡሩን ቋጥኝ ይድፈነው ምጤን ፊትሽ አላምጥም::
ዘመነኞች ፋሐ ስፓራሽ፣ እኒህ ባለምላጮቹ፣ ወንድ ሲወለድ
አይምሩም::
ምጤን በሩቅ ሰሚ እንጂ፣ አዋላጆችሽ ይቅሩብኝ፤
ጆግና ሲወለድ አይራሩም::
የሩፋኤል ፀበል ቂደርሽ ምጥ ያገላግል ነበር እሉ
ያኔ ዕንቁዕ ወላዶችሽ «እንኳን ማርያም ማረችሽ» ሲባሉ
እባክሽ ክቀድሞው ቂደርሽ እርጭኝ
በስማቸው ወኔዬ ይጋል
ለወንድ ምጤ ግልግል
በወንዶችሽ ስም ላስካካ::
በእነምኒልክ በእነሻካ፣
በአፍሪቃዊ የብዕር ፈርጥ በፀገመ ወሾይንካ::
የሞሮኮ ወራጅ ጅራት፣ ወይም ነጭ ምስጥሽ ይዘክር- - -
የሳሞሪ ቱሬን ነገር::
ሐኒባል፣ እብዱ ሙላህ፣ ሐቢብ ቦርጊዩባ፣ አብዱል ቃድር፣
የሊበያው የበረሀ አንበሳ፣ የምንለው አማር ሙክታር፣
ደግሞ ከኢትዮጵያ መንደር...
ኦሊቃ ድንግል፣ ኡመር ሰመተር፣



የወንድነትን ምስጢር፣
አፈርሽን እያሚጠጠ፣ ቀዩን ባሕር ከሚያወፍር፣
ግዮንሽ ቀለም ሆኖ፣ ታሪካቸውን ይዘክር::
እንደ እሳተ ገሞራ የሚፈልቅ፣ ሚያስጨነግፍ ዓይን ያለው፣
የደርቡሹን ሽርጥ ያስጣለው፣ የነጩን እናት ያስጠራው፣
የምጽዋችን የእሳት በር፣ እሉላ እባ ነጋ እኮ ነው::
የአጼ ቴድሮስ አቤልሽም፣ መቅደላ የፈሰሰ ደሙ፣
ይሄው እስከ አሁን ይጮኻል፣ ሰሚ አድማጭ ላጣ ወንድሙ::
የኔ ኢየሱስ ቴድሮስ...
ደሙን ቢያፈስልኝም፣ ሥጋውን ቢቆርስልኝም
አልቆረብኩበትምና፣ ይሄው ወንድነት የለኝም::
ሞትን ከእንቅልፍ ያሳነሱት፣ ቅዱስ አቡነ ጴጥሮስ፣
ሞት አልቀምስም ብለው ነበር፣ ውዳሴ ማርያም ሳላደርስ::
የሽንቁጥ ልጆች፣ አብዲሳ አጋ... በኢመዋቲ ነፍስ ወሥጋ
ሰማይ ቅጥርሽ አይችለውም የከፈሉልኝን ዋጋ::
. . . . ሆኖም . . . .
ያሁኖቹ ፋሐ ሲፓራሽ፣ እኒህ ባለምላጮቹ ወንድ ሲወለድ
አይምሩም
ምጤን በሩቅ ስሚ እንጂ፣ አዋላጆችሽ ይቅሩብኝ፣
ጆግና ሲወለድ አይራሩም::
. . . እየ እመት እፍሪቃ . . .
ምጥ ግልግሌን አይ ብዬ እንጂ ጸሎቴ እንዲህ መብዛቱ
ክንፋም ሰይጣንሽን ፈርቼ እንጂ፣ ምህላዬ መብርከቱ
ጠሚን እንዳላድር እንጂ፣ ሳይኖረኝ ምሳል በከንቱ
ፈጣሪሽ ሞኝ አይደለም፣ ፍቅሩ እንብርክኮ ካልገዛኝ፣
ሲኦል ገሐነሙን ፈርቼ፣ እምላኬ እምላኬ ካልኩኝ፣
እንጦርጦስ እንጂ ትርፌ፣ አውቃለሁ እንደማይምረኝ::
በምድርሽ አንድ አምላክ በዝቶ ፈጣሪሽ ዝም አለ ምነው?
ዋርካሽ የሰይጣን ማደሪያ፣ ተራራሽ ቤተ ጸሎት ነው::
ሁሉ ጸሎተኛ እንጂ፣ ቀድሞ አዳምን እንዳዘዘው፣
ምድርሽን የሚቆፍር ማነው?
ምድራዊ መናሽ ላይ ቆሞ፣ የህዝብሽ ልቡ እዛ! ነው::
ክርስቲያንሽ ኢየሩሳሌም ሙስሊምሽ መካ መዲና ወጣትሽ
ባሕር ማዶ ነው::
. . . . እዩ እመት እፍሪቃ . . .
እርጉዝ አይሽተው የለ
ይኸው ሳምጥ ሸተተኝ ከምጤ ጻዕር የከፋ



http://ethzare.wordpress.com

ከዳርፉር የማሽላ ገንፎ፣በግመል ሽንት ሲገነፋ፣
ሞቃዲሾ ሰይፏ ሲቀላ፣ ደም እንደ ውሃ ሲደፋ
ይህን የትውልድ ጉግ ማንጉግ፣ ይህን የመከራ አዳፋ፣
የማያገላብጥ መንሽ፣ ጉዱን የማይዝቅ አካፋ፣
ለትውልዴ ጋሬጣ ሳይሆን፣ ወዲያ ይሰባበር ይጥፋ።
ምሁር ያልሸው በቀቀንሽም፣ ቅጥርሽን ሲሻገርም፣
ግብረ ሰዶምን እንጂ፣ ሌላ ተምሮ አይመጣም።
ምነዋ እመት አፍሪቃ፣ ለምለምሽ ሆነ አሜከላ
እስከ መቼ ጠጠርሽን ልልቀም፣ የማይሞላ መጥቅሽን ላስላ?
እረኛሽ በጉን እያውቅም፣ ፀናብን የራሱ ዱላ።
የበግ ግዳዩን እየጣለ፣ ይሮክራል ብሎ ተኩላ።
በግን ከተኩላ ሲያፋቅር፣ ከነጫነጭባች ምድር፣
እርግብ ነኝ ብሎ ሲበር፣ ያስታርቅ መስሎ ሲያናቁር፣
ደጉ የሐገሬ ቁራ፣ ታዝቦ ነበር ዛፍሽ ሥር።
አፍሪቃ ያንቺ የጥፋት ውሃ፣ ይሄው እስከ አሁን
አልጎደለም።
ፈጣሪሽ ቀስቱን መልሶ፣ ቃልኪዳን አልገባልሽም።
ቁራሽ ይቆርጠው ቁጤማ፣ ያርፍበት ምድር የለሽም።
ሰላም በሌለበት አቅራርቶ፣ ቁራሽ እንደ ርግብ
አይዋሽም።
ወትሮም ቁራ ቁራ እንጂ፣ ደግ መሳይ ግርብ አይደለም።
. . . አዬ እመት አፍሪቃ . . .
ያሁኖቹ ፉሐ ሲፓራሽ፣ እኒህ ባለምላጮቹ ወንድ ሲወለድ
አይምሩም
ምጤን በሩቅ ስሚ እንጂ፣ አዋላጆችሽ ይቅሩብኝ ጆግና ሲወለድ
አይራሩም።
አያቶቻችን ጥንትም፣ ወሬ መጠረቅ ያውቃሉ።
የጭራቅ ተረት ነግረውን፣ ይሄው በፈሪ ተሞልቷል፣ ጓዳ
ጎድጓዳሽ ሁሉ።
አባቴም ተረት ሲተረትር፣ እንዲህ እንዲያ እያለ ነበር።
ታዲያ ምን ነካሽ እንቺ ምድር አንቲ አጓለ ማውታ
እንዳልነበርሽ የጥጋብ በር...
እንዴት ከቋትሽ አመድ፣ ከጎታሽ ግርድ ይከመር?
የአውድማሽ ምርት ተትረፍርፎ፣ አለሌች ውድን ሲጫኑ
አህዮችሽ ግርዱን ንቀው፣ ከምርቱ እንዳል ዘገኑ፣
ገለባ ብቻ ከምሬ፣ በሬ ለጉሜ ወቅቼ፣
ፍሬ አልባ አብቄን እፍ ስል፣ እስትንፋስ እንኳ አጥቼ፣



ስሄድ አያየሽ ዝም አልሽኝ፣ ስልቻዬን ግርድ ሞልቼ።
እንጀራ በቅርጫት ተግዞ፣ ግብር አውራጅ ተሰርቶ
እንዳልተበላ ከፊትሽ፣ የሱሪ ሽምቀቅ ተፈቶ፣
ዝም እንዳላሉ ውሾች፣ ድመቶች ካፋቸው ሲበሉ፣
አሞራች ጠግበው ከሰማይ፣ የሥጋ ቁራጭ እንዳልጣሉ፣
ጥንብ አንሳው እንኳን፣ ጥንብ ንቆ
እንዳል ሞላ ከረጢቱን፣ ከምርጥ ሥጋሽ ጠርንቆ
እኔ.. የግዮን ደለል፣ የጀማ ፏፏቴ አረፋ
እኔ.. የአያቶቼ ግርድ፣ የዘመን ውሽንፍር ዳፋ
እኔ.. የክሊማንጃሮ አውሎ፣ የኮንጎ አለሌ ፋጉሎ፣
እኔ.. የ«ኬፕ ኦፍ ጉድሆፕ»... «ባድሆፕ»...
እኔ.. የቪክቶሪያ አምባዛ...የዛዬር የቀትር ጤዛ...
እያኗኗርኩ ለኑባሬ
ቆሎ በቆኮርኪ ሰፍሬ
እንጀራ በላስቲክ ገዝቼ፣ የሳሳ እንደላስቲኩ፣
የጓያ ወጤን ወጥውጬ፣ ከመማይ ቀጭን በልኩ፣
እንጀራዬ ከወጤ ቀድሞ፣ መሶቤ ወዲያው ሲራቆት፣
በወጤ አውጥበት ሳጣ፣ ወጤን በወጤ ዋጥኩት።
. . . . ታዲያ ይህ በዚህ ሳይበቃ . . . .
ያሁኖቹ ፉሐ ሲፓራሽ፣ እኒህ ባለምላጮቹ፣ ወንድ ሲወለድ
አይምሩም
ምጤን በሩቅ ስሚ እንጂ፣ አዋላጆችሽ ይቅሩብኝ፣
ጆግና ሲወለድ አይራሩም
ጢማም ሽመግሌዎችሽ፣ ከዳካር እስከ ኤደን በር፣
ከፖርት ኤልዛቤጥ ደቡብ ጫፍ፣ እስከ ፎኒሽያን ምድር፣
እርግማናቸው እንጂ፣ ምርቃታቸው አይሰምር።
ለጣዖታቸው ስታረድ፣ የባዕር ድምፄ ሲወጣ፣
ሕጻን ልጃቸው እንዳይሞት፣ በፍርሃት ነፍሱ እንዳትወጣ፣
ትልቅ ከበሮ አስለጉመው፣ ይደልቅ ነበር ባለ ዕጣ።
እኩይ ጠንቋዮችሽም አፍዝዝ፣ አደንግዝ፣ አቅዝዝ አፈርዝዝ
መተታቸው እንጂ... መስተፋቅር፣ መስተጻምር፣ መፍትሔ
ሥራያቸው አይሰራም።
እኔም ምጤን አገላገል ስል፣ ለዛየርሽ ዳንግሌ በጌን፣ ለግዮንሽ
ቀይ ዶሮ አላርድም፣
ለደም መጣጭ አጋንንቶችሽ፣ ወርካሽ ሥር እጄን አልፀፋም።
አዎ እኮስኩስሳለሁ፣ አሁን እባ ጨጓሬሽ ነኝ።
ድምፄ በራማ ተሰምቶ፣ ክንፎቼን ከመለስልኝ፣



http://ethzare.wordpress.com

ያኔ ቢራቢሮ ስሆን ነው ንበር ክበር ምትይኝ፣::
ያኔ...ሴሰኛ አበባችዎሽ፣ በቀለማቸው ቢበስቡኝ፣
አነሱን አላዳቅልም... «ቱ!» ወለላቸው ይቅርብኝ::
ወንድነቴ ቅርናት ከሆነሽ፣ በከንቱ ካንጠለጠልኩት፣
ብልቴን እርኩሰት ቆርጦ፣ «ብር እምባሩን» ይሰበርበት::
ምጥ ግልግሌ ቀርቶ እንኳ፣ ጩኸቴ ብስናት ከሆነሽ፣
የማይጠረቃ ሞትሽ ይውሰደኝ፣ አቁማዳ ከርሱ ይሙላልሽ
እጥንቴን ጅብሽ ቆርጥሞ፣ ጥንብ እህያሽን ይብላልሽ::
እንዲህ አይደል «ወንድ» ሲማጥ
ሲጨላልም ሲደኝጉን እርያሬስ ስኑ ሲቀልጥ
በዮቶር የነፃነት ቃል እንደሙሴ እንዲያሻግር
ሽሽግ አርገው በግዮን ስር . . .
እንዲህ አይደል «ወንድ» ሲማጥ «እም» የሚያሰኝ የሚያናግር::

ኌ ኌ ኌ

«......ወንዶችን ሕጻናትስ ለምን አዳናችሁ?.......»
«የዕብራውያን ሴቶች እንደ ግብፐ ሴቶች ስላልሆኑ...አዋላጆች ሳይገቡ ስለሚወልዱ ነው::»
ዘፀአት 1፡ 18



http://ethzare.wordpress.com






የይስማዕከን ግጥሞች ስቀምሳቸው እንደ ግጥም ወለላ መጣፈጥም ብቻ ሳይሆን፣ እንደቅኔ ወይን ለማስከርም ይዳዳቸዋልኮ! አባቱ ይሙት፣ የኔ ወይን የመቋቋም ዓቅም ማነስ ይሆን? ለነገሩ ቅኔውን ከየት "ዘረፈው?" በሉ፡፡ ግዴላችሁም እንደወገኖቼ በቀለ ፋኖነት ጥበብ መዝረፍ ዓመል ሳይሆንበት አልቀረም። አቦ አሁንም በዘረፈ! አለበለዚያ ይህ ልጅ ለቅኔ "ቅልውጥ" ወደ ዋሸራ ብቅ ብሎ ይሆን? ወይስ በእንግድነት ተጋብዞ ከዋሸራ የቅኔ ማዕድ ታድሞ የተቋደሰውን ለእኛም ሊያቋድሰን ቆንጥሮ አመጣልን? ዘሩ ይለምልም!

ይስማዕከ እንቡቃቅላ ገጣሚ ነው፤ የግጥሞቹ ፍሬዎች ግን ከእንቡቃቅላ ምናብና ከልጅ ልቦና የተፈለፈሉ አይመስሉም፤ በሰብአዊ ገጠመኞች የበለጸገ ሰው የሚያንበለብላቸው የስሜት ወላፈኖች ናቸው ስለ ስመ አምላክ ጠርቼ አመሰክራለሁ፡ የግጥም "ከዓይን ያውጣችሁ" ብያቸዋለሁ፤ ቢስ እዳያይብኝ። [illegible] ይስጣችሁ" ስል መርቄም ለእናንተ ለአንባብያን [illegible] ውቃቤያችሁም እንደሚወዳቸው ውቃቤዬ ይነግረኛል።

[illegible] ታስሩ የሚጣልበት የቅኔ ጆንስ በምናብ ማህጸኑ እንደያዘ [illegible] የመለከታል፡፡ [illegible] የእኛን ክብካቤ የሚሻ የጥበብ ነፍስ [illegible] ስለሆነም ደቻን የወለዳትን የበኩር ልጁን ስማችሁለት [illegible] እንዲያስገኝ አሁንም "በድባብ ሂድ" በሉልኝ፤ አፈር ስሆን!

የሻው ተሰማ የኮተቤው

D AMH Yis
Yismake Werku
Yewend mit 2010
dfb m 2
DFB
03011126467002

http://ethzare.wordpress.com